# የምንመኘው ዲሞክራሲ እንደ ምዕራባውያኑ ቅድመ ሁኔታ ከሌለው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ያጠፋል!!

ይሄን ጽሑፍ ልጽፍ ሳስብ ግራ ዘመምና ግራ አክራሪ ፖለቲከኞቻችን (እምነተ አሥተዳደራውያኖቻችን) የምለው ነገር የሚገባቸውና የሚያሳምናቸው ወይም መልስ የሚያሳጣቸው ሆኖ እያለ በግል ችግሮቻቸው ምክንያት ሊቀበሉት ሊተገብሩት የማይፈልጉት መሆኑን ሳስብ እጅግ ሐዘን ይሰማኛል፡፡ ሁላችንም ማለት ይቻላል ዲሞክራሲያዊ (መስፍነ ሕዝባዊ) ሥርዓት በዚህች ሀገር ተመሥርቶ ማየት የማይፈልግ ዜጋ ያለ አይመስለኝም፡፡

የሚገርመውና የሚደንቀው ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ ዲሞክራሲ (መስፍነ ሕዝብ) ማለት ምን ማለት እንደሆነና ዓላማና ግቡ ምን እንደሆነ እንኳን ተራው ዜጋችን ይቅርና የግራም የቀኝም ተሰላፊ ባጠቃላይ ሁሉም ፖለቲከኞቻችንና ምሁራኖቻችን የማያውቁ መሆናቸው ነው፡፡ ይህ ወቀሳ የማይመለከታቸው ይኖሩ ይሆን? አላውቅም፡፡ የሚታወቁት ግን እንዲህ እንዳልኳቹህ ናቸውና መጀመሌ፡፡ መሆናቸውን ደግሞ ወደኋላ ትረዱታላቹህና ታገሱ፡፡

ስለ ዲሞክራሲያዊ (መስፍነ ሕዝባዊ) ሥርዓት ትክክለኛ ሥዕል ወይም ግንዛቤ ፖለቲከኞቻችን (እምነተ አሥተዳደራውያኖቻችን) አለመያዛቸው አለማወቃቸው ለሀገራችን ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) ያለመረጋጋት ችግርና ቀውስ ዋነኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ዲሞክራሲ (መስፍነ ሕዝብ) ማለት የትም ቢዘራ የሚበቅል አረም ሳይሆን እጅግ እንክብካቤና ጥበቃ የሚፈልግ፣ የተመቸ መሬት ካለገኘ በስተቀር የማይበቅልና የማያድግ አድጎም የማያፈራ ተክል ማለት ነው፡፡ ፖለቲከኞቻችን ሊገባቸው ያልቻለው ይሄ ነው፡፡

ፖለቲከኞቻችን ዲሞክራሲ በምዕራባውያኑ ዘንድ በቅድመ ሁኔታ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ እንዲሠራ እንደተደረገ ፈጽሞ አያውቁም ወይም ልብ አላሉም አላስተዋሉም፡፡ ይሄንን ችግራቸውን "በሀገራችን እንዲሰፍን እንፈልጋለን!" እያሉ ከሚያወሩት የዲሞክራሲ ዓይነት መረዳት ይቻላል፡፡ ምን ፈልገው ምን እንደሚሠሩ ጨርሶ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ኃላፊነት የሚባልን ነገር አያውቁም፡፡ ስለማያውቁም አይገባቸውም አይሰማቸውም፡፡ በተለይ ዘውገኞቹ ወይም የጎሳ ፖለቲካን አቀንቃኞቹ ያለምንም ፋታ ዘወትር ከዓይናቸው ሥር ፈጦ የሚታያቸው በግል ፍላጎት የናወዘ የግል ጥቅም ብቻና ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ኃላፊነት የሚባል ነገር አይገባውም አይሰማውም፡፡

ለመሆኑ ምዕራባውያኑ ዲሞክራሲያቸውን በምን ዓይነት የቅድመ ሁኔታ ማዕቀፍ ውስጥ ነው እንዲሠራ ያደረጉት? "ዲሞክራሲ እንደ አረም የትም የሚበቅል ተክል አይደለም! ለመብቀል ለማደግና ለማፍራት ምቹ መሬት የሚፈልግ ተክል እንጅ!" ሲባል ምቹው መሬት ምንድን ነው? መባሉ አይቀርምና እሱን ዕንይ፡- ምዕራባውያኑ ዲሞክራሲን በሀገራቸው እንዲሠራ ወይም እንዲበቅል እንዲያድግና እንዲያፈራ ያደረጉት ሊበቅል ሊያድግና ሊያፈራ የሚችልበትን ምቹ መሬት ላይ ስለተከሉት ነው እንጅ ሊበቅል ሊያድግና ሊያፈራ በማይችልበት መሬት ላይ ተክለው አይደለም እንዲበቅል እንዲያድግና እንዲያፈራ ያደረጉት፡፡
ዲሞክራሲ ሊበቅል ሊያድግና ሊያፈራ የሚችልበት ምቹ መሬትና ምቹ ያልሆነ መሬት ማለት ምን ማለት ነው? ቁልፉ ጉዳይ ይህ ነው?

ምዕራባውያን የጎሳ ፖለቲካ በተፈጥሮው ፀረ ዲሞክራሲ፣ ፀረ ሰላም፣ ፀረ ሰብአዊነት፣ ፀረ ሥልጣኔና የችግሮች ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

ስለሆነም ዲሞክራሲያቸውን ከመትከላቸው በፊት መሬቱ ላይ ዘውገኝነት ወይም ጎሰኝነት እንዳይኖር አደረጉ፡፡ ዘውገኝነት ወይም ጎሰኝነት ባለበት መሬት ላይ የፈለገ ተአምር ቢፈጠር ዲሞክራሲ ሊበቅል ሊያድግና ሊያፈራ አይችልምና፡፡ ምክንያቱም መሬቱ ለዲሞክራሲ ተክል ፍጹም የማይመች ጭንጫ ስለሆነ፡፡

አቶ ኦባማ ኬንያን በጎበኙ ጊዜ ከምዕራባውያኑ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በመቅዳት ምን ሲሉ ነበር ዘመዶቻቸውን ኬንያውያን የመከሩ? "ከጎሳ ተኮር ፖለቲካ ራቁ! የጎሳ ፖለቲካ ሀገር ያፈርሳል! ይበትናል!" በማለት ነበር አበክሮ የመከረው፡፡

በዚህም ምክንያት ምዕራባውያን ሀገራት ይሄንን ጠንቀኛ ጎሳ ተኮር ፖለቲካን ከፊሎቹ ሀገራት በሕግ እስከመደንገግ ሳይደርሱ የጋራ መግባባትን (Consensus) በመፍጠር፤ ከፊሎቹ ደግሞ በሕግ ደንግገው በመከልከል ጎሳ ተኮር ፖለቲካን ወይም ዘውገኝነትን በሀገራቸው እንዳይሠራ፣ ማረፊያ ሥፍራ እንዳያገኝ በማድረግ ፖለቲካቸው (እምነተ አሥተዳደራቸው) ሰብአዊነት ላይ፣ የዜጎች ፖለቲካዊና ማኅበራዊ መብቶች ላይ ባሉ ልዩነቶች ብቻ እንዲዘወር ወይም ፖለቲከኞቻቸው ይህን መሠረት አድርገው እንዲፎካከሩና እንዲሸናነፉ ፖለቲካዊ ምኅዳራቸውን ቀረጹ፡፡
በዚህ ቅድመ ሁኔታ ወይም ማዕቀፍ ውስጥ ነው ምዕራባውያኑ በየሀገሮቻቸው ዲሞክራሲን እንዲሠራ ወይም እንዲበቅል እንዲያድግና እንዲያፈራ ያደረጉት፡፡ ምቹ መሬት ማለት ይሄ ነው፡፡

የእኛ ፖለቲከኞችና ምሁራን ግን ሁሉን አዋቂ ነን እያሉ፣ በማየት ብቻ ብዙ ሊማሩ ከሚችሉባቸው እዚያው ከሠለጠኑት ሀገራት እየኖሩ ይሄንን ቁምነገር ጨርሶ ልብ አለማለታቸው፣ አለመረዳታቸው፣ አለማወቃቸው ዘውገኝነትን ወይም ጎሰኝነትን ማቀንቀናቸውና "የአንድነት ኃይል ነን!" የሚሉትም ሊመሠርቱት የሚፈልጉት ዲሞክራሲ ዘውገኝነትን ወይም ጎዘኝነትን የሚያስተናግድ እንደሚሆን መናገራቸው እጅግ አይደንቅም ትላላቹህ? ለነገሩ ድንጋይ የፈለገውን ያህል ዘመን ውኃ ውስጥ ቢኖር ዋና ችሎ ይወጣል? እንዲያ ነው ነገሩ፡፡

ለዚህ ነው መግቢያዬ ላይ "የሚገርመውና የሚደንቀው ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ዓላማና ግቡ ምን እንደሆነ እንኳን ተራው ዜጋ ይቅርና የግራም የቀኝም ተሰላፊ ወይም ሁሉም ፖለቲከኞቻችንና ምሁራኖቻችን የማያውቁ መሆናቸው ነው!" ስል የመረረ ወቀሳየን ያቀረብኩት፡፡

ፖለቲከኞቻችን እንዲህ ሊሆኑ የቻሉት ምናልባትም ይህ በቅድመ ሁኔታ ማዕቀፍ ውስጥ ያለ የምዕራባውያኑ ዓይነት ዲሞክራሲ ጠባብና ዕኩይነት የተሞላ የግል ጥቅማቸውን ሊያስከብር ስለማይችል ይሆናል በተፈጥሮው ፀረ ዴሞክራሲ፣ ፀረ ሰላም፣ ፀረ ሰብአዊነትና ፀረ ሥልጣኔ የሆነውን ጎሳ ተኮር ወይም የዘውግ ፖለቲካን አሁንም በተፈጥሮው ሊያስተናግደው ከማይችለው ዲሞክራሲ ላይ ሰንቅረው የማይታሰብና ሊሆን የማይችል የፖለቲካ ሥርዓት ለመመሥረት በከንቱ እየደከሙ የሚገኙት፡፡

ልንመሠርተው የምንፈልገው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የጎሳ ፖለቲካን ካስተናገደ ውጤቱ ጎሳንና ብሔረሰብን መሠረት ያደረገ የእርስ በእርስ ግጭትና እልቂት፣ የከሸፈ ዲሞክራሲና አንባገነናዊ ሥርዓትን መፍጠር መሆኑን ይሄንን መንገድ የሞከሩ ሀገራትንና ወያኔን ማየቱ ብቻ በቂ መረጃ ነው፡፡

ስለሆነም በሀገራችን የተረጋጋ ፖለቲካዊ ሥርዓት እንዲኖርና ዲሞክራሲም ያለምንም ችግርና እንቅፋት የጸና መሠረት ይዞ እንዲሠራ ወይም እንዲበቅል እንዲያድግና እንዲያፈራ ከፈለግን እንደምዕራባውያኑ ሁሉ አቶ ኦባማ "ሀገር ይበትናል! ያፈርሳል!" ያሉትን የጎሳ ፖለቲካን ሕገወጥና የተከለከለ ማድረግ የግድ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

ይሄኔ ነው ዲሞክራሲ በሀገራችን ሊበቅል ሊያድግና ሊያፈራ በሚችልበት ምቹ መሬት ላይ የተተከለ ተክል ሊሆንና ሊያፈራ ፍሬውንም ሊያስኮመኩመን የሚችለው፡፡

በሀገራችን የጎሳ ፖለቲካ የተከለከለ ከሆነ በቀጥታ ዲሞክራሲ ያለ አንዳች ገደብ በተፈለገው መጠን ሕዝቡ እንዲለማመደው፣ እንዲኖርበት ቢፈቀድለት መብቱ ቢሰጠው እንኳ በእርግጠኝነት አንዳችም አደጋ ጉዳትና ችግር ሳያስከትል መልካም ትሩፋቱን ልንኮመኩም እንደምንችል ማንም ሊጠራጠር አይገባም፡፡ በተፈጥሮው ዲሞክራሲ ሊያስተናግደው የማይችለውን ጎሳ ተኮር ፖለቲካን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስተናገድ ከሞከርን ግን ውጤቱ አቶ ኦባማ እንዳሉት ሀገርን መበተን ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

አሁን ተስፋ አደርጋለሁ ጎሳ ተኮር ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ ፖለቲከኞቻችንና "ምሁራን" ምን ያህል የጠራ የዲሞክራሲ ግንዛቤና ዕውቀት እንደሌላቸው፣ ኃላፊነት የሚባል ነገር የሚሰማቸው እንዳልሆኑ ተረድታቹሀል፡፡

ፖለቲከኞቻችን በተለይም ዘውገኞቹ የግል ጥቅማቸውን እንጅ የሀገርንና የሕዝቧን ጥቅም ስለማያስቀድሙና መናኛ የግል ጥቅማቸውን የማስከበሪያው ብቸኛ መንገድ ደግሞ ጎሳ ተኮር ፖለቲካን ወይም ዘውገኝነትን ማቀንቀን በመሆኑ የዘውገኝነትን ጎጅነት፣ ኋላቀርነት፣ ፀረ ሰላም፣ ፀረ ሰብአዊና ኢዲሞክራሲያዊነትን እንዲያውቁ ቢደረግም ፈጽሞ

ከዘውገኝነት መውጣት ዘውገኝነትን መተው አይፈልጉም፡፡ በዚህ ምክንያት የሀገራችን ፖለቲካ እንዴት ሊፈወስ እንደሚችል እግዚአብሔር ይወቀው! የጎሳ ፖለቲካን አቀንቃኝ ፖለቲከኞቻችን ሌላ ዓላማ ካላነገቡ በስተቀር የያዙት አቅጣጫ ወደ ጥፋት እንደሚወስድ እየታወቀ ሙጥኝ የሚሉበት አንድም ምክንያት የለምና እባካቹህ ተመከሩ? መሰላቹህ እንጅ ከጎሰኝነት ወጥታቹህ አንድነትን ብታቀነቅኑ እኮ የሥልጣን ፍላጎታቹህን የበለጠ ሊያሟላ ይችላል እንጅ እንቅፋት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በምንገነባው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሥልጣን ሊገኝ የሚችለው ሁሉም በየአካባቢው ሕዝብ ተመርጦ ሲመጣ ብቻ ነውና፡፡ ስለሆነም በየአካባቢያቹህ ሕዝብ ድጋፍ ከተማመናቹህ አንድነትን ማቀንቀናቹህ ሥልጣን አያሳጣቹህምና እባካቹህ ጠባብ ጎሰኝነትን እየሰበካቹህ ሕዝብን ወደ ጥፋት መምራቱን፣ መውሰዱን፣ ማሳሳቱን ትታቹህ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ተመለሱ?

ከላይ እንደጠቀስኩት የአንድነት ኃይል የሚባለውም እራሱ አንድነትን ማቀንቀን፣ ለአንድነት መታገል ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ አንድነትን ለማስጠበቅ ማንን? ለምን? እንዴት? መዋጋት መታገል እንዳለባቸው ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡
ስለማያውቁ ነው ግንቦት 7 ና ሌሎች የአንድነት ኃይል ነን የሚሉ ፓርቲዎች (ቡድኖች) ከዘውግ ድርጅቶች ጋር ከዘውገኝነታቸው ሳይወጡ እሱን እንደያዙ ከነሱ ጋር ሊጣመሩና ሊተባበሩ የቻሉት፡፡
ስለማያውቁ ነው ለሀገር አንድነትና ህልውና ቆሜያለሁ የሚለው ኢሳት ዘውገኞችን ወይም ጎሳ ተኮር ፖለቲካ የሚያቀነቅኑትን እየጋበዘ ጠባብ አስተሳሰባቸውን እንዲናኙ፣ እራሳቸውንና ድርጅቶቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ሽፋን እየሰጠና ዘውገኝነት እንዲጠናከር አሉታዊ አስተዋጽኦውን እያበረከተ ያለው፡፡

የአንድነት ኃይል ነን የሚሉ ኃይሎች ዘውገኝነትንና የዘውግ ፖለቲካን አጥፊነት፣ ፀረ ልማት፣ ፀረ ሰላም፣ ፀረ ዲሞክራሲ፣ ፀረ ሥልጣኔ፣ ፀረ ሰብአዊነትና ኋላቀርነትን በሚገባ ያጤነ የተገነዘበ የተረዳና ዘውገኝነትን ለመዋጋት ለማጥፋት የቆረጠ አቋምም የያዘ ካልሆነ በእርግጠኝነት የምነግራቹህ እነኝህ ኃይሎች የአንድነት ኃይል አይደሉም፡፡

ምን እንደሚሠሩም አያውቁም፡፡

"ዲሞክራሲያዊና የአንድነት ኃይል ነኝ!" የሚል ሁሉ ከላይ በገለጽኩት መልኩ መቃኘት ይኖርበታል፡፡
በምዕራቡ የዓለማችን ክፍል ያለው ፖለቲካም ያደረገው ይሄንኑ ነውና፡፡ በምዕራብ ሀገራት ያሉ የብዙኃን መገናኛዎች ዘውገኝነትን የሚያቀነቅን ፖለቲከኛ ቢያጋጥማቸው በምንም ተአምር ሽፋን አይሰጡትም፡፡ ሽፋን ከሰጡት የሚሰጡት ሕዝባዊ ተቀባይነት እንዳያገኝ አሉታዊ በሆነ መንገድ ነው እንጅ ሊበረታታ በሚችልበት መንገድ አይደለም፡፡
ደግነቱ ዘውገኝነት በእነኝህ ሀገራት ማረፊያ ስፍራ እንዳይኖረው አድርገዋልና ሲጀመርም እንዲህ ብሎ የሚነሣ ፖለቲከኛ የለባቸውም፡፡ በእነኝህ ሀገራት ፈጽሞ እንዲህ ዓይነት አዝማሚያ አይታይም ማለቴ ግን አይደለም፡፡ የተለየ ታሪካዊ ጉዳዮችን መሠረት አድርጎ ስፔን፣ ካናዳና ታላቋ ብሪታኒያ ችግሩ የሚታይባቸው ሀገራት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

በምዕራቡ ሀገራት "ተጨቆንኩ! መብቴ ተነፈገ! ጥቅማችንን አጣን!" የሚል ጎሳ ወይም ብሔረሰብ ካለ መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር፣ ከጭቆና ለመላቀቅ እንዲታገል የሚፈቀድለት በሰብአዊና የዜጎች መብት መከበር ማዕቀፍ ውስጥ ነው እንጅ "የእከሌ ጎሳ ነጻ አውጪ!" ምንትስ ቅብርጥስ በማለት አይደለም፡፡

የተለያዩ ጎሳዎችና ብሔረሰቦች ባሕል፣ ቋንቋና እሴቶች የሀገር ሀብት ስለሆኑና መጠበቅ ስላለባቸው ፋይዳቸው እየታየ ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል እንጅ የጎሳ ፖለቲካ ድርጅት ስላለና እነኝህ ነገሮች እንዲጠበቁለት ስለታገለ አይደለም፡፡ እኛም ይሄንን የምዕራቡን የዓለም ክፍል ተሞክሮ በመውሰድ በዘውገኝነት ወይም በጎሰኝነት ላይ እነሱ የወሰዱትን አቋምና እርምጃ እስካልወሰድን ጊዜ ድረስ በምንም ተአምር ፈውስ እናገኛለን የተረጋጋች ሀገርና ሕዝብ ይኖረናል ብላቹህ በጭራሽ እንዳታስቡ፡፡

በመሆኑም የተረጋጋች ሀገርና ሕዝብ እንዲኖረን ከፈለግን በዘውገኝነት ላይ መዝመት ግድ ይለናልና በዘውገኝነት ወይም በጎሳ ፖለቲካ ላይ እንዝመት!!! ፖለቲካችንን እንደምዕራባውያኑ ጎሳ ተኮር ፖለቲካን ወይም ዘውገኝነትን በሀገራችን እንዳይሠራ፣ ሕገወጥና ማረፊያ ሥፍራ እንዳያገኝ በማድረግ ፖለቲካችን (እምነተ አሥተዳደራችን) የዚህ ጎሳ የዚያ ብሔረሰብ ሳንል በሰው ልጅነት ብቻ ዜጎችን እኩል በሚመለከት ሰብአዊነት ላይ፣ የዜጎች ፖለቲካዊና ማኅበራዊ መብቶች ላይ ባሉ ልዩነቶች ላይ ብቻ እንዲዘወር እናድርግ፡፡

ይሄንን ስናደርግ ከችግርና ከቀውስ ጋር እስከመጨረሻው እንለያያለን!!
ነገር ግን ከቅጥረኝነት ወይም ከባንዳነት የተነሣ ይህ እንዳይሆን እንቅፋት የሚሆኑ፣ ሕዝብን ወደተሳሳተ አቅጣጫ ነድተው ገደል መክተት የሚፈልጉና ጥረት የሚያደርጉ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዳሉ ታውቆ ትግላችን ይሄንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እነደሆነ መረሳት አይኖርበትም፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com